# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 152 ሚያዝያ 6 2003 ገጽ 1


አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ከመለስ አገዛዝ ጋር እየነገዱ ያሉ የንግድና የኮንስትራክሽን ኩባንያዎችን፤ የትምህርት ተቋማትንና ታዋቂ ሰዎችን እያፈላለግን ከመለስ ዜናዊ አምባገነን ሥርዓት ጋር የሚደርጉትን ግንኙነት እንዲያቋርጡ ማስገደድ ይኖርብናል። መለስ ዜናዊና ወንጀለኛ ባልደረባዎቹ ለፍርድ የሚቀርቡበት ሁኔታ ማመቻቸት ይገባል። ጥቃታችንን በሁሉም መስኮች ማጠናከር ይገባናል። ከእንግዲህ ማፈግፈግ የለም። የጥቃት ዘመቻው ተጀምሯል። ሁሉም ለመጨረሻ ፍልሚያ ይታጠቅ!!!

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## ወያኔ የኢትዮጵያ ሳታላይት ቴለቪዥን ኢሳትን ከ3ኛ ሳታላይት ማሰራጫ ጣቢያ ላይ ለማስወረድ በጽናት እየተንቀሳቀሰ መሆኑን የኢሳት ማኔጅመንት አስታወቀ

ህዝባችን በዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ሥር የሚተዳደሩት የሃሰት ፕሮፖጋንዳ ማሰራጫዎች ከሚያሰራጩት ውጪ ምንም አይነት መረጃ እንዳያገኝ ለመከልከል የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ከውጪ ወደ አገር ቤት የሚተላለፉትን መገናኛ ብዙሃን ሙሉ በሙሉ ለመዝጋት እየተንቀሳቀሰ መሆኑን በዚህም ምክንያት ኢሳት ወደ ኢትዮጵያ የሚያደርገውን ስርጭት ካለፈው ቅዳሜ ጀምሮ ለ2ኛ ጊዜ መቋረጡን የኢሳት ማነጅመንት ለዝግጅት ክፍላችን ገለጸ።

የዛሬ አንድ አመት ገደማ በአረብ ሳት በኩል በከዩ ባንድ ስርጭቱን ወደ ኢትዮጵያና አካባቢዋ አገሮች የጀመረው ኢሳት፤ ገና አገልግሎት መስጠት በጀመረ በ3 ሳምንት ዕድሜው ከቻይና በተገዛና የሰሜን የአገራችን ክፍል ውስጥ በተተከለ የሳታላይት ሲግናል መጥለፊያ መሳሪያ መደብደብ እንደተጀመረ የሳታላይት መስመሩን ያከራየው ድርጅት በወቅቱ ለኢሳት ማኔጅመንት አሳውቋል። ለ3 ተከታታይ አመታት አገልግሎት ለመስጠት ከኢሳት ጋር የኮንትራት ውል የተፈራረመው (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## የወያኔ አገዛዝ ኢትዮጵያዊያንን በማስገደድ ቦንድ እንዲገዙ እያደረገ መሆኑ ተገለጸ

ኢትዮጵያዊያንን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአዲስ የሚለኒየም ግድብ ነጠላ ዜማ እያደነቆረ የሚገኘው ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ የተዋጣልኝ የልማት መንግስት በመሆኔ የአባይ ወንዝ ግድብ ስራን ዛሬዉኑ እጀምራለሁ በማለት በይፋ ከገለጸ ማግስት ፣ ለግድቡ የግምባታ ስራ ኢትዮጵያዊያን ገንዘብ እንዲያዋጡ ማስገደድ መጀመሩን የግንቦት ሰባት ዘጋቢ በላከልን ሪፖርት ገለጸ፤ ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ በኑሮ ውድነት ማጥ ውስጥ ገብቶ ኑሮውን መግፋት የተሳነውን ህዝብ እንዲህ እያስገደደ መዋጮ እየሰበሰበ ባለበት ሁኔታ እንደ ግል ኩባንያው ተቆጣጥሮአቸው በሚገኙት የዜና ማሰራጫዎቹ ህዝቡ በፈቃደኝነት ቦንድ ለመግዛት እየተሽቀዳደመ ነው እንዳተቀደሙ እያለ መሆኑን፤ ዘጋቢያችን ከአዲስ አበባ ከተማ በላከልን ዘገባ ገልጹአል። እንደ ዘገቢያችን ሪፖርት በተለይም በተለያዩ መስሪያ ቤቶች የሚገኙ ሰራተኞችን ለሆዳቸው ባደሩ ወኪሎቹ አማካኝነት በተዘዋዋሪ መንገድ በግዴታ እስከ አንድ ወር የሚደርስ ደሞዛቸውን እንዲከፍሉ እያደረገ መሆኑን ልጾልናል። ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## በአረብ አገር ጉልበታቸውን ሸጠው ከሚተዳደሩ ገንዘብ ለመሰብሰብ ወደ ሳኡዲት አረቢያ የተላከው ቡድን ተቃውሞ ገጠመው

በሰሜን አፍሪካ ተቀጣጥሎ የተለያዩ ዐረብ ሃገራትን እያዳረሰ ያለው የህዝብ ብሶት ፣ ቁጣና አመፅ የመላው ዓለምን ቀልብ ስቦ በሚገኝበት ባሁኑ ወቅት የወያኔ የጥፋት መልእክተኞች ቡድን ወደ ሳዑዲ ዓረቢያ ሪያድ ኤምባሲ መጉአዛቸው የግንቦት ሰባት ዘጋቢ ከስፍራው በላከልን ዘገባ አመለከተ። ሪፖርተራችን ከሪያድ በላከልን ዘገባ የዘረኛው አገዛዝ የጥፋት መልእክተኞች ወደ ሪያድ ያቀኑት ለሁለት አጀንዳዎች ሲሆን አንደኛው የኢትዮ-ሳዑዲ ባንክ በሳዑዲ ዐረቢያ በመከፈት ኢትዮጵያዊያኑ ገንዘባቸውን በዚሁ ባንክ ማስቀመጥ እንዲችሉና ሃዋላም በዚሁ ባንክ እንዲልኩ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ አዲሱን የሚለኒየም ግድብ ነጠላ ዜማ ለማስደመጥ ብሎም የቦንድ ሽያጭን ተግባራዊ ለማድረግ እንዲቻል ለዲያስፖራው ማስረዳትና ማሳመን በሚል መሆኑን ለመረዳት ችለናል ፡፡ የዘረኛው አገዛዝ መልእክተኞች ቡድኑ ሳዑዲ ዐረቢያ እንደደረሱ ከኤምባሲ ሰዎች ጋር ውይይት ከአደረጉ በኋላ በሪያድ ፣ በጅዳ እና በደማም ላሉ የኮሙዩኒቲ አመራሮች መልዕክት እንዲያስተላልፉላቸው ቅድመ ዝግጅት እንዲያደርጉ ጥብቅ መመሪያ ከኤምባሲው ተብየው ተላልፎላቸዋል፡፡

እንደዘጋቢያችን ሪፖርት ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ ከዚህ በፊት በተለያየ ጊዜ ዐረብ ሃገር ያለውን የኢትዮጵያ ኮሙዩኒቲ ለስብሰባ መጥራታቸው የተለመደ መሆኑን ነገር ግን በስብሰባዎቹ ዘወትር የሚነሱት ነጥቦች ለትግራይ ልማት የገንዘብ መዋጮ፣ ለሕዋሃት ታጋዮች መቋቋሚያ፣ ለትግራይ ትምህርት ቤት ማሰሪያና የመሳሰሉት እንደነበሩ ነገር ግን በሌሎች ክልሎች ለሚገኙ ኢትዮጵያዊያን የልማት ስራ ምንም አይነት ጥያቄ ይቀርብ እንዳልነበር አስታውሱአል።

ይሁን እንጂ ዘጋቢያችን ያነጋገራቸው አንዳንድ ሪያድ (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## በሰሜን አሜሪካ የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን የመለስ ዜናዊን ከፋፋይ ፕሮፖጋንዳ ለማሰራጨት የተላኩትን ተላላኪዎች ሴራ አከሸፉ

ባለፈው ቅዳሜና እሁድ እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር ሚያዝያ አንድ እና ሁለት ወያኔ የተለመደውን የሃሰት ፕሮፖጋንዳውን በስደት ወጪ አገር ለሚኖረው ኢትዮጵያዊ ለማሰራጨት በሰሜን አሜሪካ የተለያዩ ከተሞች ጠርቶት የነበረው ህዝባዊ ስብሰባ በየአዳራሾቹ ዘልቆ በገቡት ተቃዋሚዎች እና ከስብሰባው አዳራሽ መግቢያ ላይ ቆመው የተቃውሞ ድምጻቸውን ሲያሰሙ በነበሩ ሰልፈኞች መጨናገፉን በየከተሞቹ የሚኖሩ የግንቦት 7 ዘጋቢዎች ለግድት ክፍላችን በላኩት ዘገባ ገለጹ።

በርካታ ኢትዮጵያዊያን እንደሚኖሩበት በሚታወቀው የዋሽንግተን ዲሲ ለተጠራው ስብሰባ ንግግር ያደርጋሉ ተብሎ ካገር ቤት ከተላኩት ውስጥ ለመለስ ዜናዊ ባላቸው ታማኝነት ላልፉት 20 የወያኔ አገዛዝ ዘመናት በተላልቅ ስልጣን ማማ ላይ ካሉት ብርሃነ ገብረክርስቶስ እና አርከበ እቁባይ በተጨማሪ ለሆዳቸው በሚሰጣቸው ዳርጎ ተደልለው የገዛ ህዝባቸውን ስቃይ የሚያራዝሙትና ወገናቸውን የሚያስጨፈጭፉ ከኦሮሞ ብሄረሰብ ግርማ ብሩ ፤ ከአማራ ደመቀ መኮንን ከጉራጌ ሬዱዋን ሁሴን የመሳሰሉ ባንዳዎች ይገኙበታል።

በዋሽንግተን እና አካባቢዋ የሚኖሩት ኢትዮጵያዊያን በእልህ፤ የአገዛዝ ዘመናቸው ፍጻሜ መቃረቡ እረፍት የነሳቸው ወያኔዎችና የጥቅም ተጋሪዎቻቸው ደግሞ በጉጉት ሲናፍቁት የነበረው ያለፈው ቅዳሜ ስብሰባ ከመጀመሩ በፊት ወደ ስብሰባው አዳራሽ ለመግባት የሚያስችለውን የጥሪ ወረቀት የያዙትን እንዲለዩ መግቢያው ላይ የተመደቡት የወያኔ ጀሌዎች ይቃወመናል ብለው የሚያስቧቸውን መግባት እየከለከሉ የራሳቸው የመሰላቸውን ሲያስገቡ በበርካታ ሰው ወደአዳራሹ መምጣት ፊታቸው በፈገግታ ተሞልቶ እንደነበር ቦኋላ ግን ይደግፉናል ያሉዋቸው ሰዎች የስብሰባ አዳራሹን በተቃውሞ ሲያተራምሱት በድንጋጤ ተውጠው ለዕርዳታ የፖሊስ ትክሻ ሲንትቱ መስተዋላቸውን ሪፖርተራችን ገልጾአል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## አንድነት ለፍትህና ዴሞክራሲ ፓርቲ አንድነት መግለጫ አወጣ

በቅርቡ በተካሄደው የፓርላማ ምክር ቤት ተብየ ስብሰባ በዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ ቁንጮ በማስፈራሪያ ዛቻና ማስጠንቀቂያ የተሰጠው አንድነት ለፍትህና ዴሞክራሲ ፓርቲ አንድነት የአገዛዙን ዛቻ ከፉኛ የሚቃወምና የሚወግዝ መግለጫ አወጣ። "የጭዳ ፍየል ፍለጋ ከመወራጨት ለተገቢ የህዝብ ጥያቄዎች ተገቢ ምላሽ መስጠት" በሚል ረእስ መግለጫ ያወጣው የአንድነት ፓርቲ "በሰሜን አፍሪካ የተጀመረው ህዝባዊ አብዮት በተመሳሳይ አምባገነናዊ ጭቆና ሥር ላለ ህዝብ ከአፈና ሥርዓት ለመላቀቅ አረአያነት ያለው ተስፋ የመሰነቁን ያህል በአለማችን ዙሪያ ባሉ የአምባገነን መሪዎች መንደር ትልቅ ሽብር ፈጥሮአል ካለ በሁኣላ በዚህ ችግር ውስጥ ከሚገኙ አምባገነን መሪዎች ውስጥ 99.6 በመቶ ድምጽ በማግኘት ከህዝብ ጋር ኮንትራት ስለመፈረማቸው አብዝተው በመናገር የሚታወቁት አቶ መለስ ዜናዊ ግምባር ቀደም ናቸው" ብሏል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## የወያኔ አገዛዝ ፍርሃቱ ከቁጥጥሩ ውጭ እየወጣ ነው፣ በተለያዩ ከተሞች በጽጥታ ጉዳይ ህዝባዊ ስብሰባ ያስፈልጋል አለ

ኢህአዴግ በአዲስ አበባ እና በዋና ዋና የክልል ከተሞች የደህንነትና የጸጥታ ጉዳይ አሳሳቢነትን አስመልክቶ ሕዝባዊ ስብሰባ መደረጉ የተገለጸ ሲሆን፤ የዘረኛው አምባገነን አገዛዝ ባለስልጣናትና ሆድ አደሮች ኢትዮጵያ ውስጥ ወጣቶች የሚመሩት ሕዝባዊ ንቅናቄ እንዳይከሰት ሰግተዋል ሲል ኢሳት በትናንትናው እለት ባወጣው ዘገባው ገለጸ፡፡

እሁድ ሚያዚያ 2 ቀን 2003 ዓ.ም ከቀኑ 2:30 ሰዓት ጀምሮ የተካሄደው ሕዝባዊ ስብሰባ የወጣት ማህበራትን፣ የሴቶች ሊግን፣ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችንና የመንግሥት ሠራተኞችን ለይቶ የጠራ ሲሆን የዘረኛው አገዛዝ ከፍተኛ አመራሮች ስብሰባውን ስብሰባዎቹን መምራታቸውን ኢሳት አክሎ ገልጹአል።

የእለቱ ስብሰባ አጀንዳዎች የአካባቢና የሀገር ልማት ቁርኝት፣ የሀገርን ልማት የሚያደናቅፉ የደህንነትና የጸጥታ ጉዳዮች፣ ለወጣቶች የብድር መስፈርትና አቅርቦት፣ ወቅታዊ የዓለም ሁኔታና የኢትዮጵያ አጠቃላይ ዕድገት የሚሉ ርዕሰ ጉዳዮች ይገኙበታል በማለት ምንጮቻችን ዋቢ አድርጎ የዘገበው ኢሳት ወጣቶችን ወደ ኢህአዴግ ፓርቲ ለመመልመል መድረኩ ጥቅም ላይ ይውላል መባሉንም ገልጹአል፡፡

በዕለቱ በስብሰባ ላይ የተሳተፉት ወጣቶች ከንቁ የኢህአዴግ ፓርቲ አባላትና ካድሬዎች ጋር በአንድነት በመጠርነፍ በቅርብ ጊዜያት ውስጥ በአካባቢ ልማትና የጸጥታ ጉዳዮች ላይ ተጠሪ ሆነው እንዲንቀሳቀሱና እንዲሰሩ እየተደረገ ሲሆን ይህም በምሥራቅ አፍሪካና በመካከለኛው ምሥራቅ የዓረብ አገራት ላይ የተከሰተውን ዓይነት ሕዝባዊ መነቃቃት በኢትዮጵያም እንዳይከሰት ለመከላከል ያስችላሉ ከተባሉ ልዩ ልዩ ስትራቴጂዎች ውስጥ አንዱ ነው በማለት ምንጮቹ መግለጻቸውን ኢሳት ዘግቧል።

## የማጥቃት ዘመቻው ተጀምሯል፤ ሁሉም ለፍልሚያ ይታጠቅ!!!

የመለስ ዜናዊ አገዛዝን ለማስወገድ የሚደረገው የተባበረ የማጥቃት ዘመቻ ሚያዝያ 1 ቀን 2003 ዓም በሰሜን አሜሪካ ተጀመረ። የመለስ ዜናዊ ምስለኔዎች ሚያዝያ 1 እና 2 በሰሜን አሜሪካ የተለያዩ ከተሞች ስለ አምስት ዓመቱ "የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ" ለመስበክ እንዲሁም "በአባይ ግድብ" እንቁልልጭ ኢትዮጵያዊያንን በማማለል ገንዘብ ለመሰብሰብ ያደረጉት ሙከራ ከሽፎ የህዝባዊ አመጹ ክብሪት ተጫረ። መለስ ዜናዊ የኢትዮጵያዊያንን ትኩረት ለመሳብ ይረዱኛል ብሎ በከፍተኛ ወጪ ያዘጋጃቸው ስብሰባዎች በተገላቢጦሽ የህዝባዊው አመጹ ጅማሮ ማብሰሪያ ሆኑ።

በዋሽንግተን ዲሲ፣ ሎስአንጀለስ፣ ሚኒያፖሊስ፣ ቶሮንቶ አትላንታ፣ ዴንቨር … የትግራይ ገዢ ጉጅሌ አባላትና ምስለኔዎቻቸው ለዓመታት አይተውት የማያውቁት የቁጣ መዓት ወረደባቸው። በአባይ ግድብ ዜና ይጨፍራል ያሉት ህዝብ "በባድመ፣ በምርጫ፣ በእርዳታ እህል ያልታመነ በአባይ ወንዝ ልማት አይታመንም" አላቸው። ቦንድ ለመግዛት ይሽቀዳደማል ብለው ተስፋቸውን የጣሉበት ዲያስፖራ "በላባችን ያገኘነውን ገንዘብ ለስዊዝ ባንክ አንሰጥም" አሏቸው። "አሁንስ መለስ ጀገነ" ይላሉ የተባሉ ሰዎች "የመለስ አገዛዝ በቃ!" አሉ።

ኢትዮጵያዊያን "በቃ!!! ገዬ!!! ይአከል!!! አሎኒ!!! ዲታህ!!! ወጣንደም!!! በስ!!! ጉደስ!!!" ሲሉ በአንድነት ጮኹ፤ ጨፈሩ። ቀድሞ በጋራ ተሰልፈው የጋራ ተቃውሞ በጋራ ለማሰማት ይቸገሩ የነበሩ ወገኖች በአንድነትና በጋራ "የመለስ አገዛዝ በቃን" ሲሉ መስማት ኢትዮጵያዊያን ያኮራ፤ መለስና አሽከሮቹን ግን በእጅጉ ያሸማቀቀ ክስተት ሆነ።

በግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ እምነት ሚያዝያ 1 እና 2 በሰሜን አሜሪካና የታዩት የተደራጁ ህዝባዊ ተቃውሞዎች የአገር አቀፉ ህዝባዊው ተቃውሞ መጀመሪያ ናቸው። ከእንግዲህ ድል ሳይጨበጥ ወደ ቤት መመለስ የለም። በጅማሮው እለት የታየው የአንድነትና የእልህ ስሜት ተጠናክሮ ከቀጠለ፤ በውጭ አገራት ያለው ኢትዮጵያዊ በያለበት በዚህ መልክ ከበረታ፤ ነገ ትግሉ ወደ ኢትዮጵያ እንደሚዘልቅ እና ውጤታማም እንደሚሆን እርግጠኛ መሆን ይቻላል።

ከእንግዲህ የጥቃት ዘመቻችንን ለማፋፋም የወያኔ ሹማምንት ስብሰባ እስኪጠሩ መጠበቅ የለብንም። ከመለስ አገዛዝ ጋር እየነገዱ ያሉ የንግድና የኮንስትራክሽን ኩባንያዎችን፤ የትምህርት ተቋማትንና ታዋቂ ሰዎችን እያፈላለግን ከመለስ ዜናዊ አምባገነን ሥርዓት ጋር የሚደርጉትን ግንኙነት እንዲያቋርጡ ማስገደድ ይኖርብናል። መለስ ዜናዊና ወንጀለኛ ባልደረባዎቹ ለፍርድ የሚቀርቡበት ሁኔታ ማመቻቸት ይገባል። ጥቃታችንን በሁሉም መስኮች ማጠናከር ይገባናል። ከእንግዲህ ማፈግፈግ የለም። የጥቃት ዘመቻው ተጀምሯል። ሁሉም ለመጨረሻ ፍልሚያ ይታጠቅ!!!

**የመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝ በቅቶናል፤ አንገሽግሾናል!!!**
**በቃ!!! ገዬ!!! ይአከል!!! አሎኒ!!! ዲታህ!!! ወጣንደም!!! በስ!!! ጉደስ!!!**

● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ●

### ወያኔ የኢትዮጵያ ሳታላይት ቴለቪዥን ኢሳትን . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

አረብሳት ግዴታውን ለመወጣት ይቻለው ዘንድ ከኢትዮጵያ ግዛት በሳተላይት ስርጭቱ ላይ የሚደረገው ጠለፋ እንዲቆም ከመጠየቅ አንስቶ የተለያየ ፍሪኩዌንሲ እና ባንድ ለውጥ አድርጎ እንደነበር በስተመጨረሻም ወያኔ የሚቆጣጠረው የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን የአማርኛና ኦሮሚኛው ፕሮግራሞች ከሚሰራጩበት ትራንስፖንደር ውስጥ ኢሳትን እንደጨመረ ነገር ግን የኢሳት በአየር ላይ ከመቆየት የራሱ ፕሮፖጋንዳ ማሰራጫዎች መስተጓጎልን የመረጠው የመለስ በረከት አገዛዝ በአጥፍቶ መጥፋት እርምጃ ለ15 ተከታታይ ቀናት ከሳተላይት አገልግሎት ወርዶ እንደነበር ይታወሳል።

ኢሳት የሳታላይት አየር ጊዜ እንዳያገኝ ወያኔ ከኢትዮጵያ ህዝብ ጉሮሮ ነጥቆ ለሳታላይት አከራይ ካምፓኒዎች በጉቦ እና መደለያነት የሚረጨውን በርካታ ሚሊዮን ተቋቁሞ ታይኮም በተባለ ድርጅት በኩል ወደ አየር ተመልሶ የነበረ ቢሆንም የኮንትራት ጊዜው ሳይገባደድ ካምፓኒው በደረሰበት ዲፕሎማሲያዊ እና ፖለቲካዊ ጫና ከ4 ወራት ቦኋላ የኢሳትን አግልግሎት አቋርጧል። ከዚያ ቦኋላ ኢሳት ለ3ኛ ጊዜ በኢንቴል ሳት በኩል ወደአገር ቤት ስርጭቱን ቀጥሎ የቆየ ቢሆንም የኢሳት የሰሜን አፍሪካ ዘገባ ላይ ማተኮር ያላስደሰተውና ያስደነገጠው ወያኔ በገንዘብ ሃይል ሊገኝ የሚችል ማንኛውንም ሃይል በመጠቀም ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ በተደጋጋሚ የሞገድ ማወክ ተግባሩን ከዲፕሎማሲያዊና ፖለቲካዊ ጫናዎች ጋር አቀናጅቶ ገፍቶበታል። በዚህም ምክንያት ካለፈው ቅዳሜ ጀምሮ ለ2ኛ ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ የሚደርግው የኢሳት ስርጭት ተቋርጦአል።

የወያኔን አፈና ለመቋቋም ተብሎ በ8 የተለያዩ አጫጭር እና መካከለኛ ሞገዶች በሳምንት 3 ቀናት ጠዋትና ማታ ወደ አገራችን ስርጭት የሚያደርገውን የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮን ጨምሮ፤ የአሜሪካ ድምጽ ሬዲዮ፤ የጀርመን ድምጽ ሬዲዮ |ዶቼ ቬሌ| ፤ የኦሮሞ ነጻነት ግንባር ሬዲዮ እና የኢትዮጵያ አርበኞች ግንባር ሬዲዮም እንዲሁ ከፍተኛ የሆነ የሞገድ ጠለፋ እየተካሄደባቸው በአገር ውስጥ የመሰማት ችሎታቸው ክፉኛ የተጎዳ መሆኑ ታውቆአል።

### በአረብ አገር ጉልበታቸውን ሸጠው ከሚተዳደሩ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ውስጥ ያሉት የኮሙዩኒቲ አመራሮች እንዴት አሁን በዚህ ግዜ የኮሙዩኒቲ ስብሰባ ጥሩ ትሉናላችሁ ችግራችንን እያወቃችሁ ስብሰባ ብንጠራ ማነው የሚመጣልን በሚል ከኤምባሲ አመራሮች ጋር ግጭት ውስጥ መግባታቸውም ታውቁአል።

ዘጋቢያችን በሪያድ ነዋሪ ከሆኑ አንዲት ወይዘሮ እንደተገለጸለት ሪያድ ውስጥ የኢትዮጵያ የኮሙዩኒቲ ት/ቤት እና የኮሙዩኒቲ ካፍቴሪያ የሚገኝ መሆኑንና ከዚህ በፊት ጅዳ ውስጥ ያለ የኢትዮጵያ የኮሙዩኒቲ ት/ቤት 38ሚሊዮን ሪያል በማን እንደተዘረፈ የውሃ ሽታ ሆኖ መቅረቱን ይሄው ችግር አሁንም በሪያድ ኮሙዩኒቲ ት/ቤት በዘር በተደራጀ ቡድን ተዘርፎአል እየተዘረፈም ነው ብለዋል፡፡

ይህ በንዲህ እያለ የኮሙዩኒቲው ማህበረሰብና አመራሮች ድመትና አይጥ በሆኑበት ሰዓትና ኢትዮጵያዊያኑ ያቀረቡአቸው ጥያቄዎች መልስ ባላገኙበት ሰዓት ከኢትዮጵያ ኤምባሲ መልዕክት በቦንድ ሽያጭና በባንኩ መከፈት ዙሪያ እንነጋገር በማለት ለሪያድ ኮሙዩኒቲ አመራሮች ሲነገራቸው ወደ አልታሰበ ግጭት ውስጥ መግባታቸውን በዚህም ምክንያት ተልኮውን ይዞ የመጣው ቡድን የጀርባ ላይ ውጋት ሆኖበት ሁኔታዎች እስኪስተካከሉ እየጠበቀ እንደሆነ ዘጋቢያችን ገልጹአል፡፡

### የወያኔ አገዛዝ ኢትዮጵያዊያንን በማስገደድ ቦንድ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ዘጋቢያችን ከአዲስ አበባ፣ በተጨማሪ በአዋሳ፣ በባህር ዳርና ሌሎች ከተማዎች ያገኛቸው መረጃዎች እንደሚገልጹት ሰሞኑን በኢትዮጵያ የቦንድ ግርግር አዲስ ነጠላ ዜማ የህብረተሰቡን ጆሮ እያደነቆረ፣ መንገድና ህንጻው፣ ሳይቀር ሁሉም ስለ ቦንድ የሚያወሩ ይመስላሉ ብሏል። በዚህም መሰረት ሰራተኞች የአንድ ወር ደምወዛቸውን እንዲሰጡ፡ ነጋዴውና ባለሀብቱ የባንክ ደብተራቸው እየተበረበረ በፐርሰንት እንዲያዋጡ፡ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ከቀለባቸው ቀንሰው እንዲለግሱ፡ በአጠቃላይ የቦንድ ግዢው በህዝቡ ላይ በግድ ተጥሉአል ብለዋል፡፡ በማስከተልም እውነታው እንዲህ ሆኖ እያለ፤ ዘረኛው አገዛዝ እንደግል ንብረቱ በቁጥጥሩ ስር በሚገኙት የዜና ማሰራጫዎቹ ግን የቦንድ ግዢው በፍላጎት የተደረገ አስመስለው እያስተጋቡት መሆኑን ህዝብ እየተናገረ ያለው ግን ተቃራኒውን መሆኑን ገልጹአል።

እንደ ዘጋቢያችን ሪፖርት በምእራብ አማራ ክልል የተለያዩ ከተሞች ውስጥ ከእድሮችና ከቤተክርስቲያን ምጽዋት ሳይቀር ገንዘብ በግድ እየተሰበሰበ ለግድብ ስራ አዋጡ በሚል ሽፋን ከፍተኛ ዘረፋ እየተፈጸመ ነው በማለት የአካባቢው ነዋሪዎች መናገራቸውም ታውቁአል፡፡ ነዋሪዎቹ ባሁኑ ሰአት ኢትዮጵያዊያን ልክ በአንድ በረት ውስጥ እንደታጎርን ከብቶች ሆነናል፣ መውጫ ቀዳዳው እንዲጠብብን ተደርጉአል፣ አንዳንዶች በቀዳዳ ሾልከው ራሳቸውን ነጻ ለማድረግ ሲሞክሩ ፣ ከውጪ ያለው ጉልበታም በዱላ ይቆረቁባቸዋል፡፡ ይሁን እንጂ አንድ ቀን ይሄ በረት መሰበሩና ከውስጥ ያሉትም ከብቶች ከቁጥጥር ውጪ በሆነ መልኩ ጥሰው መውጣታቸው አይቀሬ ነው ብለዋል፡፡

ቦንድ ግዙ የተሰኘው አዲሱ የዘረኛውና አምባገነኑ መለስ ነጠላ ዜማ ከተለቀቀ ጊዜ ጀምሮ ህዝቡ የተደናገረውን ያህል ቀስ በቀስ ሁሉ ነገር ላም አለኝ በሰማይ ዓይነት ነገር ሲሆንበት በግልጽ በአደባባይ መጠየቅ መጀመሩን የተናገሩት የአዲስ አበባና አዋሳ ከተማ ነዋሪዎች ደግሞ የወያኔ ነጠላ ዜማ በየከተማው የስብሰባ አጀንዳ ሆኖ ዉይይት እንዲደረግበትና በቦንድ ስም ገንዘብ እንዲያመጣ፡ መጀመሪያ በፍላጎት እንዲጠየቅ፡ የሚያቅማማ ከሆነ እንደ ግዳጅ እንዲጣል ሰፊ ዘመቻ መከፈቱን ይናገራሉ።

በተለይም በአዋሳ በአንዱ ቀበሌ የሆነውን ለዘጋቢያችን የገለጹ ግለሰብ እንዲህ ብለዋል፡፡ ስብሰባው በዓባይ ወንዝ አጭር ታሪክ ተከፈተና ጠቅላይ ሚኒስትሩ በፓርላማ ስለዓባይ ግድብ ያወሩት የቃል ለውጥ እንኳን ሳይደረግበት በአንድ ካድሬ ቀረበ። ከዚያም ቦንድ ግዙ ተባለ፡፡ እጅ የሚያወጣ ጠፋ። ካድሬው ድጋሚ ጠየቀ። ምንም የለም። በቃ! መንግስት ተነስቷል። እናተም ተነሱ። ቦንድ መግዛት አለባችሁ ብሎ ማፋጠጥ ጀመረ። በመካከሉ አንዲት እናት ምርር ብለው፡¨ በቁማችን ሞተናል። አሁን ምን ሁኑ የምትሉን? ስላልተቀበርን ነው?¨ ብለው በለቅሶ እየታጀቡ መናገር ሲጀምሩ የቀበሌ ካድሬ ያስቆማቸዋል። ተሰብሳቢው በጉምጉምታ ካድሬው ተቃወመ። እናት ቀጠሉ¨ ሁለት ልጆች አሉኝ። ተረከቡኝ። የማበላቸውን አጥቼ በረሃብ ይታመሙብኛል። ከየት አምጥቼ ነው የምትሉትን የምገዛው? ከፈለጋችሁ ወስዳችሁ እሰሩኝ። በቃ!¨ እናት እዬዬ አሉ። በአደራሹ ያለው በሙሉ ማለት በሚቻል መልኩ አብሮ አነባ። የሴትዬዋ ጥያቄ፡ እሮሮና ብሶት የሁሉም ነበር።የሁሉንም ብሶት እናት ተነፈሱት። ለቅሶውን ግን በጋራ አቀለጡት። አዳራሹ በሀዘን ጸጥ ረጭ አለ። መድረክ ላይ ያሉት ካድሬዎችም ሀዘኑ የመታቸው ይመስላል። እናት አሁንም ለቅሶ ላይ ናቸው። የሚያባብሏቸውም እያለቀሱ¨ተው እንጂ!¨ ይላሉ። አንድ የዩኒቨርሲቲ መምህር ብድግ አሉና¨እኔና ባለቤቴ ደምወዝተኞች ነን። እንኳን ተርፎን ቦንድ ለመግዛት መሰረታዊ ቀለባችንን ለሟሟላት ከማንችልበት ጊዜ ላይ ነን።¨ አሉ። ተመሳሳይ አስተያየት ተደጋግሞ ቀረበ። ግን የስብሰባው መንፈስ ተናግቷል። ሰው ሁሉ በሀዘን ቅጭም ብሏል። እናት አሁንም እያነቡ ናቸው። ገንፍሎ የውጣው ብሶት መቆም አለቻለም። ስብሰባው በዚሁ ተበተነ። ከመድረክ፡ ስብሰባው ሌላ ቀን እንደሚካሄድ ተነግሮ ተዘጋ። እናት በሰዎች ተከበው ከአዳራሹ ወጡ ብለዋል፡፡

# የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ባለሙያዎች ማህበር በ1996 ዓ.ም ባዘጋጀው ርዕይ 2020 የውይይት መድረክ የቀረበ (በዶ/ር ታደሰ ብሩ)

(ክፍል 5 ካለፈው ሳምንት የቀጠለ - የመጨረሻ ክፍል)

## 7. የኢትዮጵያ ልሂቃን የት ናቸው? ወዴትስ እያመሩ ነው?

ክቡራትና ክቡራን! በእስካሁኑ ንግግሬ አፅንኦት ለመስጠት የሞከርኩት ፍሬ ሃሳብ ጥሩ ሕገ-መንግሥት፣ ሕጎችና፣ መንግሥታዊ መዋቅሮች መኖራቸው እጅግ ጠቃሚ ቢሆንም እነዚህ ስላሉ ብቻ ሰላም፣ ዲሞክራሲና ልማት የማይመጡ መሆኑን ነው:: ሕገ-መንግስትን፣ ፌደራላዊ አደረጃጀትን፣ ፕሬዚዳንታዊ ወይም ፓርላሜንታዊ አስተዳደርን ከሌሎች መማርና መዋስ እንችላለን፤ ዜጎችን ከዚያ ማምጣት ግን ፈጽሞ አይቻለንም::

በ1980ቹ መጨረሻ እና በ1990ቹ መጀመሪያ የምሥራቅ አውሮፓ አገሮች ልሂቃን «ሕገ-መንግስት ኮረጅነናል፤ መንግሥታችንንም በታወቁ የዲሞክራሲ መሥፈርቶች አኳያ አዋቅረናል፤ እናስ ሰዎቹ ለኮረጅነው ሕገ-መንግሥቱ ምቹ ሆነናል ወይ?» እያሉ ደጋግመው ራሳቸውን ሲጠይቁና ሲወቅሱ አስተውለናል::

ኢትዮጵያና ምሥራቅ አውሮፓ ውስጥ የለዉጥ ማዕበል የነፈሰው በተመሳሳይ ጊዜ ነው:: ዛሬ ግን የትናየት ተራርቀናል! የኢትዮጵያ ልሂቃን ራሳቸውን መዉቀስ ገና መጀመራቸው ነው:: ብዙዎቹ አሁንም እንደ ድሮው ሁሉ ራሳቸውን «የቀለም ቀንድ»፣ «ምጡቅ»፣ ወዘተ፣ እያሉ ማሞካሸቱን የቀጠሉበት ይመስላል:: እርግጥ ነው አንዳንድ አበረታች ጅምሮች እየታዩ ነው::

ከአመታት በፊት ክፍሉ ታደሰ «ያ ትዉልድ» በተሰኘ ተከታታይ መፅሐፉ የኢትዮጵያዊያዉያን «ቦልሸቪክ» ልሂቆች ሕልምና ዕጣ ፈንታ አስነብቦናል::

ሳያስቡትና ሳይዘጋጁበት መንገድ ላይ የወደቀን ሥልጣን አንስተዉ በራሳቸዉም፣ በአገራችንም፣ ላይ አስከፊ ጉዳት ያደረሱት ወታደራዊ ልሂቃንን ታሪክ ደግሞ ዳዊት ወ/ጊዮርጊስ በ«የደም እንባ»፤ ዘነበ ፈለቀ ደግሞ በ«ነበር» ተርከዉልናል::

ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም ለ1997 እንቁጣጣሽ ስጦታ «የክህደት ቁልቁለት»ን አበርክተውልን የአንድ ልሂቃን ቡድን የብዙ ዓመታት የተቀነባበረ ሴራን እንድናይ ረድተውናል::

የዚህን ጽሑፍ ረቂቅ ወደማገባደድ በደረስኩበት ወቅት የአቶ አንዳርጋቸው ጽጌን «ነጻነትን የማያውቅ 'ነፃ አዉጭ': ስልጣኔ፣ ዲሞክራሲ እና ብልጽግና: የፖለቲካ ልሂቃን ሚና በዘመናዊት ኢትዮጵያ» በሚል ርዕስ ያሳተሙት መጽሐፍ በድንገት እጄ ውስጥ ገባ:: ይህንን መጽሐፍ ጨርሼ ለማንበብ ጊዜ አላገኘሁም፤ ሆኖም በነበረኝ የተጣበበ ጊዜ ገረፍ ገረፍ አድርጌ ያየሁትም ቢሆን («ኤሊት» ለሚለው የእንግሊዘኛ ቃል «ልሁቅ» እና «ልሂቃን»ን መጠቀምን ጨምሮ) ረድቶኛል:: ጊዜ አግኝቼ መጽሐፉን በርጋታ ማንበብ ብችል ኖሮ ጹሑፌን በእጅጉ ያዳብርልኝ እንደነበር አልጠራጠርም::

እነዚህና ሌሎችም ያልጠቀስኳቸዉ ሥራዎች መልካም ጅምሮች ቢሆኑም በቂ ሊባሉ ግን ፈጽሞ አይችሉም:: ስለኢትዮጵያ ልሂቃን ያለን እውቀት እጅግ በጣም ውስን ነው:: የምርምር ሥራዎችም በዚህ መንገድ የሄዱ አይመስለኝም::

የኢትዮጵያ ልሂቃንን ለማጥናት የሚከተሉት ነጥቦች ጠቃሚ ይመስሉኛል::

1. የኢትዮጲያ ልሂቃን በጣም መበታተናቸው ሳያንስ እርስ በርሳቸው በእጅጉ የሚፃረሩ፣ አንዱ ሌላኛውን ከምድር ገጽ ለማጥፋት ከመረረ ጥላቻ ጋር የተነሱ መሆናቸው፣ አገራችን ዛሬ ለምትገኝበት አሳዛኝ ሁኔታ የዳረገን ይመስለኛል:: የመጠፋፋቱ ትግል በደርግ ጊዜ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሶ የነበረ ሲሆን አሁንም መልኩን እየቀያየረ ቀጥሏል:: ኢትዮጵያዊያን ልሂቃን በአገራዊ ጉዳዮች የጋራ መግባባት ላይ ካልደረሱ በስተቀር ይህ የጥላቻና የመጠፋፋት ፖለቲካ በቀላሉ የሚቆም አይመስለኝም::
2. የአገራችን ልሂቃን በየራሳቸው ቡድን ውስጥ በርዕዩተ-ዓለም የተሳሰሩ መሆናቸው ሌላው ባህሪያቸው ይመስለኛል:: እያንዳንዱ ቡድን የሚመራበት የራሴ የሚለው ርዕዩተ-ዓለም አለው:: ልሂቃኖቻችን ርዕዩተ-ዓለማቸዉን ምሉዕ አድርገዉ ስለሚወሰዱ ከዚያ ወዲያ ዕዉቀት ላሳር እስኪሉ ድረስ ችኮ ደብተራ ከመምሰላቸዉም በተጨማሪ በቡድን ዉስጥ የሚነሱ ለዕድገት አስተዋፅዖ ሊኖራቸዉ ይችሉ የነበሩ ልዩነቶች በአግባቡ እንዳይስተናገዱ አድርጓል:: ትንንሽ ልዩነቶች በጠላትነት የሚያስፈርጁ በመሆኑ ተቃዉሞን በግልፅ ከመናገር ይልቅ ዙርያ ጥምጥም፣ አግቦ፣ ተረቦችና ድብቅነትን አስፋፍቷል:: ዛሬ በሥልጣን ላይ የሚገኙ ልሂቃኖቻችን ንግግሮች በተረብ የተሞሉ መሆናቸዉ፤ ሥልጣን ላይ እንኳን ሆነዉ ሕቡዕ የገቡ የሚመስለዉ በዚህ ምክንያት ይመስለኛል:: (ለማስረጃ ያህል እስከ ሕዋህት መስንጠቅ ድረስ ግማሹ ያህል የፖለቲካ ቢሮ አባላቱ በሕዝብና በሚዲያው የሚታወቁ አልነበሩም፤ በየጊዜዉ ታትመዉ የሚወጡ ፖሊሲ መሰል ሰነዶች ደራሲያቸዉ አይታወቅም) የኢትዮጵያ ልሂቃን የተበታተኑ ሁነው በየራሳቸው ጎጆ ውስጥ ደግሞ በርዕዩተ-ዓለም መታጠራቸው ራሳቸውንም አገራችንንም በእጅጉ ጎድቷል:: አንዱ የሌላውን ሃሳብ ለመረዳት ጥረት እንዳያደርግ ዓይኖቻቸውንና ጆሮዎቻቸውን ሸፍኖታል:: ይህ ደግሞ በመካከላቸው ያለው አለመተማመንና የጥላቻ ፖለቲካ ሥር እንዲሰድ አድርጓል::
3. የኢትዮጵያ ልሂቃን (ሁሉም ማለት ይቻላል) ለእኩልነትና ፍትህ እንታገላለን ባይ ኢጋሊታሪያን መሆናቸው ሌላው አቢይ ባህርይ ነው:: እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ሊብራዝሊዝም ርኩስ ሃሳብ ተደርጎ ሲብጠለጠል ነበር:: እንታገልለታለን፣ እንወክለዋለን የሚሉት የታችኛው የሃብት ወለል ላይ ያለው የኅብረተሰብ ክፍል ልሂቃን የሚያነበንቡትን «ድጋም» ለመረዳት በእጅጉ የሚቸገር በመሆኑ ወደፊት የምትመሰረተውን ማርና ወተት ለሕዝቧ በእኩል የሚፈስባትን የተስፋይቱን ምድር እውን ለማድረግ የታዘዘውን የሚፈጽም ትጉህ ምዕመን እንዲሆን ተደርጓል:: ምናልባት ከኢ.ድ.ሕ. ልሂቃን በስተቀር ሁሉም የግራ ፖለቲካ አራማጆችና የኮሚኒዝም ፍቅር በልባቸው ያደረ ነው:: ቀደም ሲል እንደጠቀስኩት በተመሳሳይ እምነቶች መካከል ያለው ቅራኔ በተለያዩ እምነቶች መካከል ካለው ቅራኔ የባሰ ይከራል:: ከ1960ቹ ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ እያወዛገበ ያለው ከጎሳ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ብሄረሰብ፣ ብሔር፣ ሕዝብ፣ ሕዝቦች፣ ወዘተ፣ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ «ዘዉገኝነት» ያሉት አስተሳሰብ ከኢትዮጲያዊነት፣ አህጉራዊነትና ዓለም-ዓቀፋዊነት ጋር እየተጋጨ ልሂቃኑን እርስ በርስ ክፉኛ አላትሟል፤ እያላተመም ነው:: የሚገርመው እነዚህ ዘውገኛ ልሂቃን ራሳቸውን «ዓለም-ዓቀፋዊ» ታጋይ ማድረጋቸው ነው::
4. «የኤርትራ ጥያቄ» ሌላዉ የኢትዮጵያ ልሂቃን መወዛገቢያ ሆኖ ቆይቷል:: የኢትዮጵያ አካል ሁናም እያለ፣ አገርነቷ ከታወቀላት በኋላም የኤርትራ ጉዳይ ከኢትዮጵያ ልሂቃን ጭንቅላት መውረድ አልቻለም::

የኢትዮጵያ ልሂቃን እጅግ የተበታተኑና እርስ በርሳቸው የሚፃረሩ፣ በየራሳቸው ጎጆ ውስጥ ደግሞ በርዕዮተ-ዓለም የተሳሰሩ መሆናቸውን ገልጫለሁ:: በሌሎች አገሮች እንደታየው እንዲህ እንደኛ የተበታተኑና እርስ በርሳቸው የሚፃረሩ ልሂቃን ወደ ስምምነት የሚመጡት አንድም የጋራ የውጭ ጠላት ሲኖር ወይም የአክራሪዎች ተደጋጋሚ ሽንፈት ልሂቃኑን መሃል ላይ ሲያሰባስባቸው ወይም ደግሞ በሰጥቶ መቀበል ድርድሮች ነው::

የኢትዮጵያ ልሂቃን ወራሪ ጠላት በመጣ ጊዜ ልዩነቶቻቸውን ወደጎን በመተው በአንድነት መነሳታቸው የተለመደ ነው:: በቅርቡም በኤርትራ ወረራ ወቅት ታይቶል:: የሚያሳዝነው ግን ሁሌም ይህ ስምምነት ከድል በኋላ በኖ የሚጠፋ መሆኑ ነው:: የዚህን ምክንያት በጥልቀት መመርመር ይኖርብናል:: ድህነትና ረሃብም እንደ ጋራ ጠላት ሊያስተባብሩን ይገባ ነበር፤ ግን አልሆነም:: ለምን? እኔ አላውቅም:: ምርምር የሚሻ ጉዳይ ነው::

መሃል ላይ መሰባሰብ የተባለው ኢትዮጵያ ውስጥ የቱ ዳር፣ የቱ መሃል፣ እንደሆነ መለየት አስቸጋሪ ነው:: በመጀመሪያ ደረጃ አብዛኛዎቹ ልሂቃኖቻችን ምንጫቸው የግራ ፖለቲካ በመሆኑ ፖለቲካችን እስከዛሬም ወደግራ ያዘመመ ነው:: በሌላ በኩል ደግሞ የግራ ፖለቲካ ከደረሰበት ስብራት ማገገም አልቻለም:: በዓለም ላይ ሊብራሊዝም ሁሉን አቀፍ ድል ተቀዳጅቷል:: ፍራንሲስ ፉኩያማ ታሪክ ባበቃበት ዘመን ነው ያለነው ያለዉ ለዚህ ነው:: እርግጥ ነው ፉኩያማም እንዳስተዋለው የግራ ፖለቲካ በቀላሉ አይሞትም፤ መፍጨርጨሩ፣ መንፈራፈሩ፣ መንፈራገጡ አይቀርም:: ሩሲያ ውስጥ ሚካኤል ጎርቫቾቭ «ፕሪስትሮይካ» (እንደገና መገንባት) የሚባል የተሃድሶ መድሃኒት ቀምሞለት ነበር፤ አልሆነም:: እኛ አገር ደግሞ «አብዮታዊ ዲሞክራሲ» የሚባል ሌላ መድሃኒት ተቀምሞለታል:: እሱም እጅግ ውስን ለሆነ ቦታ ማደንዘዣነት /local anesthesia/ ከማገልገል አልፎ የግራ ፖለቲካን መታደግ አልቻለም፣ አይችልምም:: ከወቅቱ የአለም ፓለቲካ አንፃር ከታየ የግራ ፖለቲካ አጠቃላይ ውድቀት ላይ ነው:: ኢትዮጵያ ከዓለም ዉጭ መሆን አይቻላትም፤ እናም የኢትዮጵያ ልሂቃን ሳይወዱም ቢሆን ሊብራሊዝምን ማጥናት ግድ ይሆንባቸዋል:: እርግጥ ነዉ እድሜ ልክ ያጠኑትንና ያመኑበትን መተው በጣም ፈታኝ ነገር ነው:: የእድሜ ልክ ሌኒኒስቶችና ማኦኢስቶች በድንገት ሊብራል እንሁን ሲሉ የሚፈጥሩት አስቂኝ ትርኢት ሳስተዉል "unlearning is more difficult than learning" የሚለው ማን እንደተናገረው የማላውቀው አባባል ትክክለኛነትን አደንቃለሁ::

በተለያዩ የዓለም ክፍሎች እንደታየዉ ኢትዮጵያም ዉስጥ የርዕዩተ ዓለም ፓለቲካ አላዋጣ ሲል ዘረኝነትና አክራሪ አማኝነት በከፍተኛ ፍጥነት እየተስፋፉ ነው:: ይህ ደግሞ ከርዕየተ-ዓለሙ ትግል የባሰ አውዳሚ ነው:: ሳሙኤል ሃንቲግተን የስልጣኔ ግጭቶች /civilizational clashes/ የሚላቸውን ዓይነት ዘርና ሃይማኖትን መሠረት ያደረጉ ግጭቶች አገራችንን ያሰጓቷል:: በዘርና በሃይማኖት ስንቧደን የሚደርሰው ውድመት ምነው እንደ ድሮኣችን በ«ላብአደር» እና «ወዛደር» ተጣልተን በተቧቀስን የሚያስብል ሊሆን ይችላል::

በአንድ በኩል ለእርስ በርስ መፋጀታችን ምክንያት ሆኖ በቆየው የግራ ፖለቲካ ላይ ኪሳራ መድረሱና ወደ ሊብራዝም ማምራታችን የማይቀር መሆኑ በግሌ ቢያስደስተኝም፣ በአንፃሩ ደግሞ የርዕዮተ-ዓለሙን ክፍተት የዘር ፖለቲካና አክራሪ ሃይማኖቶች እንዳይተኩት እሰጋለሁ::

ይህም ሆኖ ግን ተስፋ ሰጭ ጅምሮች አሉ:: አንዱ ከላይ የጠቀስኩት የግራ ፓለቲካ ላይ የደረሰዉ አጠቃላይ ኪሳራ አገራችንም ዉስጥ ሊብራል አስተሳሰቦች እንዲያብቡ መንገድ ከፍቷል:: አሁን ሶሻል ዲሞክራቲክ ፓርቲዎች ወደ ፓለቲካዉ መድረክ እየመጡ ነዉ:: ከጥቂት ጊዜ በኋላ ደግሞ የቀኝ ፓለቲካ አራማጆች ይመጡና የኢትዮጵያ ፖለቲካን ወደ ቀኝ ስበዉ መሃል ላይ ያለዉን ፕሮግራም (centerist) አሸናፊ ያደርጉታል የሚል ተስፋ አለኝ:: ሌላዉ ተስፋ ሰጭ ሁኔታ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የኢትዮጵያ ልሂቃን ወደ ሶስት ቡድኖች የመሰባሰብ ዝንባሌ ማሳየታቸዉ ነዉ:: ይህ ዝንባሌ በፓርቲዎች መቀናጀት ብቻ ሳይሆን በፕሮግራሞቻቸዉም ግልጽ እየሆነ መምጣት ጀምሯል:: የግንቦቱ ምርጫ ዉድድር - ለምሳሌ - ባብዛኛዉ በሶስት ቡድኖች መካከል ነዉ የሚሆነዉ:: የምርጫ ወቅት መቀናጀቶች ወደ ሁለት ቢወርዱ ኖሮ በጣም የተሻለ ይሆን ነበር፤ ሶስትም ግን ትልቅ መሻሻል ነዉ::

ለኢትዮጵያዊያን ልሂቃን መግባባት ያላቸው ሌላ አማራጭ «ሰጥቶ መቀበል» ብዬ የጠራሁት ድርድር ነው:: አሁን በሥልጣን ላይ ያለዉ ልሁቅ በድርድር ሥልጣኑን መልቀቅ ወይም ማጋራት ይፈልጋል? ከድርድሩ ምን ሊያገኝ? አሁን ምንድነው ያጣው? እነዚህ ጥያቄዎች ለእኔ በጣም ከባዶች ናቸው፤ ግምቶቼን ግን ላስፍር::

አሁን በሥልጣን ላይ ያለው ልሁቅ የህጋዊ ተቀባይነት /ligitimacy/ ችግር አለበት:: ገነባሁ የሚለው ዲሞክራሲ ወደ መቶ በመቶ የተጠጋ የምርጫ ድጋፍ ውጤት «እያመጣበት» የተቸገረ ይመስለኛል:: ከበርሊን ግንብ መፍረስ ወዲህ መቶ በመቶ የሕዝብ ድጋፍ የሚያኮራ ሳይሆን የሚሳፍር ሆኗል፤ ዘጠናም፣ ሰማንያም፣ ሰባአምስትም፣ ጥሩ አይደለም:: አሁን በሥልጣን ላይ ያለው ልሁቅ በምርጫ ወቅት የሚያገኘዉ ድጋፍ ወደ ሰባ በመቶ አካባቢ ወርዶለት በነፃና ፍትሃዊ ምርጫ የተመረጠ መንግሥት ነዉ መባል የሚፈልግ ይመስለኛል። ለዚህ ደግሞ ጥቂት ወንበሮችን ማጣት ይፈቅዳል የሚል እምነት አለኝ:: አስቸጋሪዉ ጥያቄ ለዚህ ምን ያህል ወንበሮችን ማጣት ይፈቅዳል? የሚለዉ ይመስለኛል:: «ይኸንንማ መራጩ ሕዝብ ነዉ የሚወስነዉ» እንደማትሉኝ ተስፋ አለኝ፤ ምክንያቱም ሥልጣን ላይ ያለዉ ልሂቅ የምርጫዉን ዉጤት መቆጣጠሪያ ስልቶችን ማበጀቱ ግልፅ ነዉና:: በመሆኑም «ሕዝቡ ማንን ይመርጣል?» ሳይሆን «አሁን በሥልጣን ላይ ያለዉ ልሂቅ ለተቃዋሚዎቹ ልሂቃን በየት አካባቢ ምን ያህል መቀመጫ መልቀቅ ይፈልጋል?» የሚለዉ ጥያቄ የበለጠ ነባራዊ ሁኔታዎችን ያገናዘበ ይመስለኛል:: ሕዝቡ በምርጫ የመወሰን መብቱን ገና ሙሉ በሙሉ እጁ ዉስጥ አላስገባም:: መራጩም፣ ተመራጩም፣ አስመራጩም ለምርጫ ስነ-ምግባር (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## የትግራዩ ገዢ ጉጂሌ ቁንጮ መለስ ዜናዊ 121 ኢትዮጵያዊያንን በአሸባሪነት ሊከስ መሆኑ ተዘገበ

ባለፈው አንድ ወር ውስጥ የመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝ በጅምላ ካሰራቸው እና ለጊዜው ቁጥራቸው ከታወቁት 200 በላይ እስረኞች ውስጥ  አንድ መቶ ሃያ አንዶቹ በሽብርተኝነት ክስ ሊመሰረትባቸው እንደሆነ ሮይተርስ በትናንትናው ዕለት ባወጣው ዘገበ ገለጸ። መለስ ዜናዊ ባለፈው ማክሰኞ መጋቢት 27 በራሱ አምሳል ጠፍጥፎ ለሰራው ፓርላማ ተብዬ ሸንጎ ንግግር ባደረገበት ወቅት በሰላማዊ ትግል የፖለቲካ አላማቸውን እውን ማድረግ እንችላለን ብለው በይፋ የሚንቀሳቀሱትን ተቃዋሚ ፓርቲዎች ለማስፈራራት በግፍ የታሰሩት አባላቶቻቸው ሽብር ለማካሄድ የሚንቀሳቀሱ ናቸው በማለት እንደወነጀላቸውና የሱን ልብ ትርታ እየለኩ ፍርድ ለሚሰጡ ፍርድቤቶቹ እንደሚያቀርባቸው ዝቶ እንደነበር ይታወቃል።

መለስ ዜናዊ እንደግል ድርጅቱ በሚፈነጭበት ፓርላማ ውስጥ ባለፈው ማክሰኞ ባደረገው እንቶ ፈንቶ ንግግር አብዛኛውን የጥያቄና መልስ ክፍለ ጊዜውን ያሳለፈው የመድረክ ፓርቲ አባል የሆኑትን ድርጅቶች በመሳደብና በማስፈራራት እንደነበረ የተከታተሉት የመድረክ ፓርቲ አመራር አባላት ሰለሰውየው ድንፋታ የየራሳቸውን አስተያየት ስጥተዋል። የአንድነት ለፍትህና ለዲሞክራሲ ፓርቲ አመራር አባል የሆኑት አቶ አንዱአለም አራጌ ከፓርላማ ምክር ቤት ተብየው ስብሰባና ድንፋታ በሁአላ በሰጡት አስተያየት “መለስ ስለደነፋ የሚቀነስም ሆነ የሚጨመር ነገር የለንም” ያሉ ሲሆን፣ በሰሜን አፍሪካ ተጀምሮ በርካታ አምባገነን መንግስታትን በማስደንበር ላይ ያለው ህዝባዊ አመጽ በኢትዮጵያም ሊከሰት ይችላል በሚል ግምት የኢህአዴግ ባለስልጣናት በርካታ እርምጃዎችን ሲወስዱ ቆይተዋል ማለታቸውም ታውቁአል፡፡ አቶ አንዱአለም ስለ ትግራዩ ገዢ ጉጂሌ አገዛዝ ሲናገሩ የወያኔ የመጀመሪያውና ውጤት አልባ የሆነው የማስቀየሻ ስልት “በመሰረታዊ የፍጆታ እቃዎች” ላይ የተደረገው የዋጋ ተመን ሲሆን የኤርትራን መንግስት በጦርነት ከስልጣን እናወርዳለን፣ አባይን ገድበን የሃይል ማመንጫ እንገነባለን፣ የቴሌ የዋጋ ታሪፍ ቀንሰናል የሚሉ ትልልቅ ርዕሰ ጉዳዮችን በሚዲያ በሰፊው በመንዛት የህዝቡን የትኩረት አቅጣጫ ለማስለወጥ ቢሞክርም ሳይሳካ ቀርቷል ብለዋል፡፡ በመቀጠልም እነዚህን በመሣሠሉ የማስቀየሻ ስልቶች በሀገሪቱ ሊከሰት ይችላል ተብሎ የሚገመተውን ህዝባዊ አመጽ ለማክሸፍ የማይቻል መሆኑን የተገነዘበው ወያኔ የተቃዋሚ ፓርቲዎችን በተለይም የመድረክ አባላትን ለእስር ዳርጓቸዋል፡፡ ይሁን እንጂ የሚዲያው ፕሮፓጋንዳ፣ የማስቀየሻ ስልቶቹና የእስር እርምጃዎቹ ህዝባዊ አመፁን ከመፍራቱ ጋር ስለ መያያዙ በግልጽ ሲናገር አልተደመጠም ብለዋል፡፡

በአንድነት ፓርቲ ላይ የተሰነዘረውን ዛቻ አስመልክቶ የፓርቲው ዋና ፀሐፊ አቶ አንዱለም አራጌ እንደገለፁት «መለስ ፍርሃት ውስጥ መሆኑን አረጋግጡአል፡፡ ንግግሩም የሚያሳየው ከዚህ በፊት የሚሄድበትን የተለመደ መንገድ ለመተግበር እንደተዘጋጀ ነው» ብለዋል፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ተግባር ጠቃሚ አለመሆኑን «የፈለጉትን ማድረግ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን በእኛ ላይ የሚወስዱት እርምጃ ከችግር አያድናቸውም፡፡ ጥያቄው የህዝብ ሆኖ ሳለ የተቃዋሚዎች አጀንዳ ለማድረግ ከመሞከር ይልቅ ራሳቸውን ገምግመው ለመታረም ቢሞክሩ የተሻለ መፍትሄ ነው፡፡» ሲሉ መምከራቸው ታውቁአል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ሂዩማን ራይትስ ዋች በመባል የሚታወቀው የሰብአዊ መብቶች ተከራካሪ ተቁአም፣ በበኩሉ የወያኔ አገዛዝ በቅርቡ ወደ እስር ቤት የወረወራቸውን የኦህዴድና መድረክ አባላት ያሰረው በፖለቲካ አቁዋማቸው ምክንያት ነው፣ እናም ባስቸኩአይ ከእስር ቤት እንዲፈታቸው በማለት መግለጫ ማውጣቱ ይታወሳል። ዓለም ዓቀፉ የሰብዓዊ መብቶች ተሚጋች ሂዉማን ራይትስ ዎች  ሎንዶን የሚገኘዉ የድርጅቱ ጽህፈት ቤት የአፍሪቃ ጉዳይ ተወካይ ከዶቿ ቬለ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ የኢትዮጵያ መንግስት በሰብዓዊ መብቶች ከበሬታ ረገድ ጥሩ ስም እንደሌለዉ በመግለፅ እሳቸዉ የሰብዓዊ መብቶች ጉዳይ በማንሳታቸዉ ከኢትዮጵያ መባረራቸዉን ማመልከታቸው ይታወቃል።

## በአዲስ አበባና በሌሎች የኢትዮጵያ ዋና ከተሞች ከተሞች  የተነሱ ጥሪ ወረቀቶች መበተናቸው ቀጥሉአል

በኢትዮጵያ ላይ የተጫነው ግፈኛና ዘረኛ አገዛዝ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ከኢትዮጵያዊያን ትከሻ ላይ ተሽቀንጥሮ ይውድቅ ዘንድ ግፊቱና ህዝብንም ለዚሁ ትግል የማያነሳሳ ጥሪ መቅረቡ ተጡዋጡፎ መቀጠሉን የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን  ባወጣው ዘገባ ገለጸ።

እንደ ኢሳት ዘገባ በአዲስ አበባ ከተማ ከተበተኑት ጽሁፎች ውስጥ አባይ ወንዝን በላያችን ላይ ያለውን የአምባገነንነት ቀምበር ካስወገድን በሁአላ እንሰራዋለን የሚል  እንደሚገኝበት ተገልጹአል።

ከበርካታ ቀናት በፊት በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የተለያዩ ቀስቃሽ ወረቀቶች በየግድግዳው እንደሚለጠፉና ሲበተኑም እንደነበር በተደጋጋሚ የተዘገበ ሲሆን ሰሞኑን ደግሞ በቃ የሚሉ ጽሁፎ በየመንገዱ ተበትነው እንደሚገኙ ይህንም ወረቀት ማን እንደበተነ አጋልጡ በመባል ሴተኛ አዳሪዎች እየታሰሩ መሆኑን ኢሳት ምንጮቹን በመጥቀስ ዘግቡአል።

ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ በተለይም የሰሜን አፍሪቃው ህዝባዊ አብዮት ከተቀሰቀሰ ወዲህ በሃገር ውስጥ ያለው እንቅስቃሴ እጂግ እያስፈራውና እያስጨነቀው እንደመጣ ሲዘገብ የቆየ ሲሆን ከዚህ ጭንቀት መውጫ መንገድ አድርጎ እየወሰደ ያለው ርምጃም ንጹሃን ዜጎችን በጂምላ ወደ እስር ቤት ማጎር እንደሆነ በርካታ የዜና አውታሮች የዘገቡት መሆኑ ይታወቃል።

ከስድስት ኪሎ ወደ ጊዮርጊስ በሚወስደው መንገድ ላይ በሚገኘው የሃብተ ጊዮርጊስ ድልድይ (አፍንጮ በር ድልድይ) ላይ ሞት ለወያኔ የሚል ጽሁፍ በትላልቅ ፊደላት ተጽፈው እንደነበር መግለጻችን ይታወሳል፡፡ በራሪ ወረቀት በከተማ ውስጥ የመበተኑ ሥራ ተፋፉሞ በመቀጠል ሰሞኑን በመርካቶ ውስጥ እየተበተነ እንደሆነ ለማረጋገጥ ተችሎአል።

## በሰሜን አመሪካ የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን የመለስ ዜናዊን . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ስብሰባው ሊጀመር ሲል በግርማ ብሩ አማካይነት የ ዕለቱ ተናጋሪዎች ማስተዋወቁ እንደተፈጸመ አንድ ያልተጠበቀ ድምጽ ብድግ ብሎ ”እስከዛሬ በወያኔ ለተጨፈጨፉት ሰማዕታት የህሊና ጸሎት ሳይደረግ ስብሰባውን መጀመር አይኖርብንም” በማለቱ ስለወያኔ 5 አመት ትራንስፎርሜሽን እቅድ እና የሰሜን አፍሪካው አብዮት ስጋት የፈጠረው የሚላኒዬም ግድብ ለመደስኮር ባህር አቋርጦ የመጣው ቡድንና ጀሌዎቻቸው በድንጋጤ እንደተዋጡ ትንሽ ቆየት ብሎም ፤ ”መለስ ዜናዊ ዜጎችን እየገደለ፤ እያሰረ እና በፍርሃት እያሸመደመደ  የምትደሰኩሩት ልማት ለማን ነው? እስከዛሬ በየአደባባዩ ለተጨፈጨፉት ተጠያቂ የሆናችሁት የወያኔ አባላት ፍርድ ቤት የምትቀርቡት መቼ ነው? ግርማ ብሩ ሆይ አንተ በትውልድ ኦሮሞ ነህ፤ የገዛ ወገኖች ላይ እየተፈጸመ ስላለው ሰቆቃ ምን ይሰማሃል? ብርሃነ ገብረክርስቶስ ሆይ ያኔ መንግሥትህን ወክለህ እዚህ አሜሪካን አገር አምባሳደር በነበርክበት ወቅት ከኤርትራ ጋር ውጊያ አካሂዳችሁ በርካቶችን ካስጨፈጨፋችሁ ቦኋላ  አለም አቀፍ ፍርድቤት ሄዳችሁ ”ባድሜ ለኛ ተወስናለች” ብለህ ነበር ዛሬስ ባድሜ የማን ናት ትላለህ ? የሚሉ ከባባድ ጥያቄዎችን አንዱ ተስብሳቢ በማቅረባቸው ንዴቱ የገነፈለው ብርሃነ ገብረክርስቶስ ድምጽ ማጉያውን ብድግ አድርጎ ”በተፈጠረው ሁከት ምክንያት ስብሰባውን መቀጠል ስላልተቻለ ስብሰባው እዚህ ላይ ተዘግቶአል” በማለት ተስብሳቢውን መበተኑን ለማወቅ ተችሎአል።

እንደ ዋሽንግተን ዲሲው ሁሉ በሌሎች ትላልቅ ከተሞች ተጠርቶ የነበሩት ስብሰባዎች ከሞላ ጎደል በተመሳሳይ ተቃውሞ እንደተጨናነቀና በዚህም ምክንያት አንዳቸውም የታለመለትን አላማ ከግብ ለማድረስ እንዳልቻለ ከደረሰን ሪፖርት ለመረዳት ተችሎአል። በካናዳ አገር በቶሮንቶ ተጠርቶ የነበረው ተመሳሳይ ስብሰባ በከተማው የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን በወሰዱት እርምጃ እንዲሁ ሳይሳካ እንደቀረ ወደ ስብሰባው ለመግባት ሂደው የነበሩት ከተቃዋሚዎች በተወረወሩ የበሰበሰ እንቁላል እንደተደበደቡ ዘጋቢያችን አስታውቆአል።

ብርሃነ ገብረክርስቶስ በሚንስቴር ዴታነት ማዕረግ ለሃይለማሪያም ደሳለኝ በታኮነት ተመድቦ ወደ አገር ቤት ከመመለሱ በፊት በአሜሪካና በበልጂዬም የወያኔ አምባሳደር በመሆን ያገለገለ  በተለይም አሜሪካን አገር በነበረበት ወቅት ከባለቤቱ ጋር በነበርበት አለመስማማት ፍርድ ቤት ቀርቦ በስሙ ባንክ ተቀማጭ የነበረ 40 ሚሊዮን ዶላር እንዲያካፍል ሲጠየቅ  ”ገንዘቡ የኔ አይደለም ለጠቅላይ ሚንስቴራችን በአደራ የተቀመጠ ነው በማለት ቃሉን ሰጥቶ እንደነበር በወቅቱ በሰፊው መዘገቡ ይታወሳል።

## አንድነት ለፍትህና ዴሞክራሲ ፓርቲ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

በመለስ ዜናዊ ድንፋታና ዛቻ እንደማይበግር ወይም  ከያዘው አላማ ዝንፍ እንደማይል በመግለጫው የገለጸው አንድነት ፓርቲ ”የኢትዮጵያን ህዝብ ጥቅም በዘፈቀደ አሳልፈው በመስጠት ህዝብ የሚያውቃቸው እነ አቶ መለስ ዛሬ ደርሰው ራሳቸውን የኢትዮጵያ ህዝብ አለኝታ አድርገው ለማቅረብ የሚሞክሩበት ተውኔት ከመናቅ ውጭ አንዳች ትርፍ እንደማያስገኝላቸው ልብ ሊሉት ይገባል” በማለት ካስጠነቀቀ ቦኋላ የሰሜን አፍሪካን ህዝቦች ለህዝባዊ አብዮት ያነሳሳው ችግር በከፋ መልኩ በኢትዮጵያችን ውስጥ ተንሰራፍቶ ይገኛል ብሎአል። በመጨረሻም ፣ ህዝብ ኡኡታውን የሚሰማለት ይፈልጋል፣ እስካሁን ኢሃዴግ መራሹ መንግስት የኢትዮጵያን ህዝብ ችግር ከማባባስ ባለፈ ማቃለል አለመቻሉ ግልጽ እየሆነ መጥቷል። ለህዝብ ብሶት ባስቸኳይ ምላሽ ስጡ፣ በአንድ ወይም በሁለት ፓርቲዎች ከማሳበብ፣ ተቆጥባችሁ፣ ጊዜና ህዝብ ለሚጠይቋቸው ጥያቄዎች፣ ያለማቅማማት ባፋጣኝ ምላሽ ስጡ፣ ሰበብ አስባብ ፍለጋ ከመወራጨት፣ ለተጨባጭ የህዝብ ጥያቄዎች ተጨባጭ መፍትሄዎች መስጠት ላይ እንድታተኩሩ እንመክራለን በማለት የወያኔን ቁንጮዎች መክሮአል።

## የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ባለሙያዎች ማህበር . . . (ከገጽ 3 የዞረ)

ተገዥ አይደሉም:: ለዚህም ነዉ የሚቀጥለዉ ምርጫ ዉጤት በአብዛኛዉ በገዢዉ ልሂቅ ፍላጎትና ፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ነዉ የሚል ግምት ያለኝ::

ይሁን እንጂ በታሪክ ዉስጥ ተደጋግሞ እንደታየዉ አፈና ረገብ ሲል ያልታሰቡ ፍንዳታዎች ይመጣሉ:: እናም የሚቀጥለዉ ምርጫ በሰላም ከተጠናቀቀ አሁን በሥልጣን ላይ ያለዉን የልሂቃን ቡድንን ሲሶዉን ያህል የፓርላማ መቀመጫዎችና የአዲስ አበባን አብላጫ ወንበር ያሳጣዉ ይሆናል የሚል ግምት አለኝ::

ይህ ግምቴ ምኞትም ጭምር ነዉ:: ይህ ከተሳካ «ጠንክረን ተንቀሳቅሰን ቢሆን ኖሮ ለካንስ መንግሥትን በምርጫ መለወጥ እንችል ነበር» በሚል ቁጭት ልሂቃኖቻችን ለ2002ቱ ምርጫ ሰፊ ዝግጅት ማድረግ ከወዲሁ ይጀምራሉ:: ሕዝቡም በምርጫ ላይ ያለዉ ዕምነት ከፍ ይላል፤ በፓለቲካ ላይ ያለዉ ጥላቻ ይቀንሳል::

ይህ መልካም ምኞት እንዲሰምር ከአሁኑ ቢያንስ የሚከተሉት ተግባራዊ መሆን ይኖርባቸዋል::

1. ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችን ማክበር፤
2. መግባባት፣ መቻቻልና መደራደርን መልመድ፤
3. መራጭም፣ ተመራጭም፣ አስመራጭም ለምርጫ ሥነ-ምግባር ተገዥ መሆን፤
4. በተለይ በሥልጣን ላይ ያለዉ የልሂቃን ቡድን የአገርን ጥቅም ማስቀደም፤
5. ልሂቃኖቻችን ዲሞክራሲያዊ አስተሳሰብ፤ ጽንፈኝነት፣ አክራሪነት፣ ጥራዝ-ነጠቅነት፣ ጎሰኝነት፣ አለመሆኑን በመረዳት ልዮነቶችን በማጥበብ ለጋራ ጥቅም በጋራ መሥራትን ሲለምዱና የመሃለኛዉን የፓለቲካ መስመር አሸናፊ ማድረግ ሲችሉ ነዉ::

እነዚህ ነገሮች ካሁኑ በተግባር ላይ ከዋሉ የ2002፣ 2007፣ 2015 እና 2017 ምርጫዎችን እንዳንዱን ከቀደመዉ የበለጠ ዲሞክራሲያዊና የበለጠ አሳታፊ እንዲሆን ያደርጉታል::

ይህ በተግባር ተረጋገጦ ከቀጠለ በ2017 የምርጫ ክርክሮች የድህነት፣ የረሃብ፣ የብሐረሰብ፣ የድንበር፣ የወደብ ጉዳዮች በጭራሽ አይነሱም:: ይልቁንስ ያኔ የሚያጨቃጭቁ አጀንዳዎች የአፍሪካ ቀንድ ፌዴራል መንግሥት እና የአፍሪካ ኅብረት ሥልጣን እስከምን ድረስ ይሂድ የሚሉትና ከግሎባላይዜሽንና ኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ይሆናሉ:: እናም የ2020 ኢትዮጵያ ሰላምና ዲሞክራሲ የሰፈነባት፤ ልማት የተፋጠነባት፤ ልሂቃኖቿ ልዩነቶቻቸዉን በዉይይትና ድርድር የሚፈቱባት፤ ኅብረትና ፋክክር የተመጣጠኑባት አገር ትሆናለች::

ግምቴ ፋርሽ ሁኖ የግንቦቱ ምርጫ ከተጨናገፈ ግን ኢትዮጵያ የሚገጥማትን መከራ ማሰብ እንኳን ይሰቀጥጣልና ስለዚህ ምንም ማለት አልፈልግም::

**ስላዳመጣችሁኝ አመሰግናለሁ::**


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**
**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**
**በ 7140፣ 7175፣ 7185  KHZ በ 41 ሜትር ባንድ እና በ 6100  KHZ በ 49 ሜትር ባንድ**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ፣ ሐሙስ እና ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት እስከ 3፡30፤ እንዲሁም ከምሽቱ 2 ሰዓት እስከ 2፡30 የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።



**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org